# ሰሞኑን በፓልቶክ

## ቁጥር 7

ከበልጅግ አሊ

ሰሞኑን ፓልቶክ በፖለቲካው ፍጥነት ሲታመስ ከርሞአል። ከጥንፍ አድርባይ እስከ ጥንፍ ዘረኛ፣ ከቱባ ፋሽሽት እስከ የወጣለት ዴሞክራት፣ ከማይረባ እንግዴ ልጅ እስከ ቆራጥ ጀግና፣ ሁሉም በየተራቸው ቀርበው ሃሳባችን ለመሸጥ በተለያዩ የፓልቶክ ክፍሎች ተገኝተው፣ ግማሾቹ የማያውቁትን ሲቀባጥሩ፣ ግማሾቹ ደግሞ በጣም በበሰለ ሁኔታና በፅኑ አቋም የራሳቸውንን ምንነት በየዘርፉ ሲያሳውቁን ነበር።

በዚች በትንሽ ቀናት ውስጥ ፓለቲካው ከምን ተነስቶ እስከምን እንደደረሰ ለመጥቀስ ትልቅ ጥናትና እውቀት ያስፈለፍገዋል። ሰሞኑን በፓልቶክ ከሰለሞን ከዳልኝ መካድ ወይ ጉድ ብለን ሳንጨርስ ፣ ክደቱ ሶስተኛው መዳናገሪያ መንገዴ ብሎ ሌላ የማደሪያ ፖለቲካ ይዞ ብቅ አለ። እነዚህ ሁለቱም በወያኔ በሚመራው የሲቪሊቲ ክፍል ቀርበው ለወደፊት ለሀገራችን ያላቸውን ራዕይ፣ በቅድሚያ ደግሞ በወያኔ በኩል በጥሩ ሁኔታ ይሸጥልናል፣ለራሳችን ሆድ ይጠቅመናል፣ የሚሉትን አቅርበው ሳይጨርሱ አቦይ ስብሃት ቀርቦ የጭቃ ጅራፉን እያወናጨፈ ፣ እንዴት ወዴት ወዴት ብሎ እነዚህን የእንግዴ ልጆች ስለወያኔ የማያውቁትን ከመስበክ አስታግሶልናል።

ስብሃት ግልፅ አድርጎ ወያኔን አሳምረው በቆንጆ ቀለም ሊስሉት ለሞከሩት ሆድ አምላኩዎች የወያኔን ምንነት በመንገር ሁለተኛ ወደ ፓልቶክ እንዳይደረሱና የማያውቁትን እንዳያለፈልፉ አድርጎ እርግጡን ነግሮቸዋል፣ ወያኔ የተነሳበትን ዛሬም ያልተለወጠውን አቋሙን ገልፆ ኩም አድርጎልኝ ሄዶል። አንዳንድ በየፓልቶኩ የግንቦቱ ድል አልፋልና ለሚቀጥለው ምርጫ እንዘጋጅ የሚሉትን፣ እስር ቤት ያሉ መሪዎቻቸውን፣ መድረሻቸው ያልታወቀውን ጓዶቻቸውን፣ የረሱትን በሙሉ ብሎም የወያኔ ፍርፋሪ ይወድቅልኛል ብለው የሚጠብቁ እንከፍ ፖለቲከኞችን አሳፍሮኝኛል። ብትፈልጉ ታዘቡኝ እንጂ ይህ አቦይ የሚሉት ዘረኛ እንዴት እንዳስደሰተኝ ልደብቃችሁ አልፈልግም።ስብሃት የአባቴን ብለቅ ይቆማምጠኝ ብሎ ምሎ ግልፅ የሆነ የወያኔን አቋም በማውጣቱ ስንቱ ሆዳም፣ አስቀያሚዋል ልጅ በቆንጆ ጭንብል ተመልከቱ ሲሉን የነበሩትን ፣ ወያኔ የኢትዮጵያን ድንበር አስጠባቂ ነው ሲሉ የነበሩትን ፣ እስቲ አንዲት ስንዝር ወደ ኤርትራ ብሎ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ፣አፈርና ወርቅ ነን ብሎ፣ ልዩነታችንን አጉልቶ ነግሮናል። የወያኔን ዘረኝነት አሁንም ያለቀቀው ወደፊትም የማይለቀው መሆኑን ግልፅ አድርጎልን አልፎአል። በተለይ ወያኔ ሚሌኒየሙን በማክበር የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ አንድ ሽህ አስገብቶታል ሲሉን የነበሩትን ሆዳሞችን አራት ነጥብ አሲዞልናል።ስለዚህ በፖለቲካ አዋቂዎች በሰፊው የተፃፈ ስለሆነ ብዙም አዲስ ነገር መፃፍ አይቻልም።

በሲቪሊቲ የወያኔ ክፍል ውስጥ የሚገኘው የስድብ መለኪዬ እንደሚመለክተው እዚህ ክፍል ውስጥ የሚታደሙትም ሆነ የሚጋበዙት ኢትዮጵያን ለመከፋፈል፣ የዘር ልዩነትን ፈጥረው እርስ በርስ ለማጣላት፣ ያልተደረገውን ተደረገ እያሉ የወያኔን ፓሮፖጋንዳ ለመንዛት፣ እኛ ከሞትን በኃላ ሰርዶ አይብቀል በሚለው የሆዳሞች መፈክር ስር የተሰበሰቡና ወደ ፊት ወያኔ ላይ አንድ ነገር ቢደርስ ከወደዚሁ የእርስ በርስ ግጭቶችን ለማስነሳት አሁኑኑ ዝግጅት ለማድረግ ቆርጠው የተነሱ ናቸው።የሚሰደበው ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ነው።ኢትዮጵያውነት ትምክህተኝነት ነው የሚሉ ዘረኞች በሆዳሞች ታጅበው እንደሚገኙበት የስድብ መለኪየዬ ያሳያል።

በስብሃት ተደንቀን ሳናበቃ የብዙ ግዜ ምኞተችን ሊድስልን ነው ብለን ጮቤ የረገጥንበት ታላቅ ርዕስ ፓልቶክን ሞላው። በውጭ አገር የሚገኙ የቅንጅት ደጋፍዎች በመካከላቸው ያለውን ቅራኔ መፍታታቸው በሰማን ግዜ ፓል ቶክ በህዝብ እንደገና ተሞላ። ሁላችንን ተሯሩጠን ቀድመን ጋቢና ተቀምጠን ቃላ መጠይቅ ለመፈለግ በየክፍሉ ተሯሩዋጥን። እኔ በበኩሌ የስድብ መለኪያዬን እሲቪሊቲ ክፍል ውስጥ በቋሚነት አስቀምጨው ለመሄድ ዝግጀት ላይ ነበርኩ።ምክንያቱም እርቅ ከወረደ ሌላ ክፍል አያስፈልግም ብዬ አምኜ ነበር። በብዙዎቹ ክፍሎቸች አንደኛው ችግር ተፈታ አሁን የሚቀጥለው ከህብረት ጋር መስማማት ነው የሚለው አስተሳሰብ ነበር ጎልቶ የሚሰማው። ገና ውይይቱ ሳያልቅ በአንዳርጋቸው በህዋስ ያደራጃቸው ክፍሎች ማጉረምረም ጀመሩ። ምንም አደል ባንዴ አይስተካከልም ብለን ማጉረምረሙን እረስተን ስለ ወረደው ሰላም አውግተን ሳንጨርስ ከቃሊቲ ሌላ ደብዳቤ መጣ ተባለና እንደገና ታመስን። አዳዲስ የቅንጅት መሪዎች ስም ዝርዝር ቀረበልን።ይቀበሉታል አይቀበሉትም የሚለው ጥያቄ ነበር የወቅቱ አነጋጋሪ ነጥብ። አወጣን አወረድን ፣ አሞገስን ፣ሰደብን ፣ የቅዳሜውን ስብሰባ እንጠብቅ ብለን ተለያየን። ቅዳሜ ሌላ አዲስ የቅንጅት መሪዎች መመረጣቸውን ሰማን ለትንሽ ግዜ እንደ ክረምት ፀሐይ ብልጭ ብላ የነበረው ተስፋችን በደመና ተሸፈነች። የስድብ መላኪያን ከወያኔ ክፍል በአስቸኳይ ወደ ድሮ ..... ሸንጎ ወደምለው ክፍል ወሰድኩት። እዚህ ላይ ስሙን መጠቀም ለምን

አቆም ትሉኝ ይሆናል። ወዳጄ የሆኑ ሰዎች ይህንን ስም ለጠቅላላው የክፍሉ ታዳሚ መስጠት ትክክል አደለም ብለው ስለወቀሱኝ እኔም ሁኔታውን ተመልክቼ ስሙን ለግዜው ተውኩት እንጂ በዛ ሽንጎ የሚሰራውን ለተመለከተ ስሙ ተገቢ ገንቢ ሂስ እንጂ ስድብ ነው አይልም።ለትንሽ ቀናት የተፈጠረው ደስታ የሃዘን ደመና ዋጠው።ስድብ የተለመደውን ክፍል የማይለቅ በሽታው መሆኑ ግልፅ ወጣ።ዶክትር ታዬና ኢሕአፓ ተወገዙ።

የስድብ መለኪዬ እንደሚያሳየኝ ከሆነ ዶክተር ታዬ ድሮም የንፅሁ ኢደትዮጵያውነቱን እዛው ክፍል እንደተገፈፈ የሚታወስ ሲሆን ( ስሞኑን በፓል ቶክ ንፅህ ዚትዮጵያዊ ማነው የሚለውን ፅሁፌን ደብተራው ላይ ስለሚገኝ ለመመልከት ይቻላል) በአሁኑ ግዜ ደግሞ የአንደኛ ተሰዳቢነቱን ቦታ ይዞል። እዚህ ላይ ኢሕአፓ ሁለተኛ ቦታ ተተክቶአል።የዶክተር ታዬ የዶክተርነት ዲግሪው ተወቅሶ ወደ ቄስ ትምህርት ቤት ተመልሶ የፓለቲካ ሁሁ እንዲያጠና ተወስኖአል። ዶክተር ታዬ በኢሕአፓነት በከፍተኛ ደረጃ ተጋልጦአል።

በዚህ ክፍል ውስጥ ለማንኛው ጉዳይ ተጠያቂው ኢሕአፓ ነው ፣ ከባልና ሚስት ጠብ እስከ ታላቅ የፓለቲካ ውሳኔ በዛ ክፍል የሚገኙት ታዳሚዎች እስካልተስማሙበት ድረስ በየስድባቸው መካከል ኢሕአፓ እስካልተሰደበ ቀኑ አይነጋም አይመሽም። በተለይ አንዳንዶቹ የሰነበተባቸው በሽታ ይመስላል።አንድ ጊዜ በቀይ ሽብር ጊዜ ነው።አንድ ከርቼሌ የቆየ የታሰረ ሰው ሁልጊዜ ሳን ጆርጅ ሻይ ቤት እንዴት ነው ብሎ ይጠይቀኛል። አሁን ይህ የምተለው ሻይ ቤት የለም እለዋለሁ ። እንደገናም እንደገናም ይጠይቀኛል። ታዲያ አንድ ቀን ምርር ብሎኝ ለምንድነው ይህንን ጥያቄ የምትጠይቀኝ ብዬ ጠየቅሁት። ወንድሜ ከሱ ሌላ ምንም ስለማናውቅ ነው አለኝ። እንደዚሁም እነዚህ የደርግ ካድሬ ፖለቲከኞች ከቀይ ሽብር ግዜ ጀምሮ የሚያውቁት ኢሕአፓን መግደል፣ መግረፍ፣ መስደብ፣ ስለሆነ ሌላ አማራጭ ለነዚህ ቦዘኔዎች የላቸውም። ስሞኑን ደግሞ የተጠናወታቸው ጋኔል ተነስቶባቸዋል መሰል በኢሕአፓ ላይ አዶከብሬቸውን ጀምዋል። ይህ መቼም አንዳርጋቸው ባቋቋመው ህዋስ የስራ ክፍፍል ውስጥ በተሳዳቢነት ለተመደቡት ስድቡን የሚሰጣቸው ከከፍተኛ አመራራቸው እንደሆነ ግልፅ ነው። አንዳንዶቹ አልፈው አልፈውም ኢንጅነር ሀይሉን መሳደብ ጀምረዋል። እኔ በዚህ በአካባቢዬ ያሉትን ስመለከታቸው ስራ የማይሰሩ የወጣት የእርዳታ ጡረተኞች ናቸው። ከኤርትራ በሚሰጣቸው መመሪያ ወደፊት የቅንጅት መሪዎቹን ቢሰድቡ ምንም አይደንቀኝም።ምክንያቱም ምልክቱን ከወዲሁ እያየሁት ነው።

በውጭ ያለው ቅንጅት በሚታመስበት ግዜ ከየት ይሁን ከየት የማይታወቅ ወሬ አገሩን ሞላው። የቅንጅት መሪዎች ሊፈቱ ነው ተባለ። መፈረምና መውጣት ይችላሉም ተብሎ በየቦታው ተናፈሰ። ፓልቶክም በህዝብ ሙልት አለች። ብዙ ተወያየንበት። ግን ተጨባጭ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም። እርግጡን እያወቅን የመጣነው የወያኔ ባለስልጣናት ሁኔታውን እንደማያውቁት መናገር ሲጀምሩ ነው።በውስጥም ይሁን በውጭ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ይህንን ለምን ጉዳይ እደተጠቀሙት ብዙ ነገር ሊነገር ይችላል። ዋናው ነገር ግን አሁንም እንደበፊቱ እንደተሸወድን ነው እኔን የሚሰማኝ። ወያኔን ማመን ከእባብ እንቁላል እባብ እንደመጠበቅ ነው። ወያኔ በየጊዜው በውጭም ይሁን በውስጥ ግፊቱ ሲበዛበት አንድ ሁኔታ ይፈጥራል። እኛም ቅን አንጀት ነንና በወያኔ ወጥመድ ውስጥ ቶሎ እንወድቃለን።ወያኔ ተመልሱ ይስቅብናል። ቆርጠን በአቋማችን መቀጠል እንጂ ሌላ የሚያዋጣን አይኖርም።

ሌላው ታላቅ ዜና ነው ብዬ የማስበው የስዬ አብርሃ ጉዳይ ነው።ሲቪሊቲ ክፍል ከዐይጋ ፎረም ጋር በመሆን እንዲፈታ ቅስቀሳ ተጀምሯል ። የሰጡት ምክንያት ይህ ግለሰብ ብዙ ለወያኔ ያገለገለ ነውና ይቅርታ ሊደረግለት ይገባል የሚል ነው።ለኔ ይህ አቋም ድንቅ ዘረኝነት ነው ። ታምራት ላይኔ ለወያኔ አልሰራም ማለት ነው ወይስ የነርሱን መመዘኛ አያሟላም? እነዚህ ዘረኞች የዘር ልጓማቸው እየጎተታቸው ነው እንጂ በሁለቱ መካከል ምንም ልየነት የለም። ይህ በጣም የሚሳየኝ የአሁኖቹ ሆዳሞች እንዴት ብለው ነው ለዚህ ለዘረኛ መንግስት የሚያድሩት? ከታምራት መማር አይችሉም ? ከኢትዮጵያ ህዝብ ተነጥው ከወያኔ ጋር ቢቆሙም ማንም እንደማያስታውሳቸው አይገባቸውም? ዛሬ ስዬ ብቻ ተነጥሎ ይፈታ ማለታቸው የሚገርም ነው።

ሌላው የሚገርመው እነ ገብሩ አስራት ፓርቲ ሊያቋቋሙ ማሰባቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።ተሳክቶላቸው ካቋቋሙ እንግዲህ ተቃዋሚ መሆናቸው ነው። ተቃዋሚዎችሽ እንደተቃዋሚ ይመለከቱዋቸዋል ወይ ነው ጥያቄው። አቋማቸውስ የድሮ ስህተታቸውን አውቀው አስተካክለው በኢትዮጵያ አንድነት ላይ በማይጠራጥር ሁኔታ መግለጫ መስጠትን ይጠይቃል። መቼም የያዛቸው አባዜ አለቅ ብሏቸው ያው የተለመደውን የዘር ስም ከሰጡት ከድጡ ወደ ማጡ ነው የሚሆንባቸው። ካልሆነም ግን የሚከተላቸው ላያጡ ይችላሉ ። ነገሩን እንደው አነሳሁት እንጂ ድርጅት በመቀያየር የተካኑ ስንት እንዳሉ ይታወቅ የለም። እነገብሩ አስራት ሌሎች ተቃዋሚዎች አብረዋቸው እንዲሰሩ ከተፈለገ በወያኔ ውስጥ ሆነው ያጠፉትን ጥፋት አምነው ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል። የዘር ፖለቲካ

እንደማያዋጣ ለማመናቸው ግልፅ የሆነ መግለጫ በየፓልቶኩና በየሚድያው ላይ ቀርበው ማስረዳትም ይኖርባቸዋል ። በተለይም ደግሞ በትግራይ አስረው ያስቀመጠዋቸውን እንደነ ፀጋዬ ደብተረውን የመሳሰሉትን የት እንዳደረሱ በግልፅ ማስታወቅ አለባቸው። በኢትዮጵያውያን ደም የተጨማለቁ ከሆነ ግን ፍርድ እንጂ ህብረት ውስጥ መግባት  የለባቸውም ባይ ነኝ። አለበዘዚያ ግን የወያኔ ጠላት ነኝ ያለውን ሁሉ የምንቀበል ከሆነ ትግሉ እጫፍ ላይደርስ ይችላል።

ስሞኑን በፓልቶክ ስንታመስ ነው ከረምነው ምን እንደሚጠብቀን አናውቅም። በየክፍሉ ግን ክፍሉን በጥሩ አቀራረባቸው ታዳሚዎችን ለመሳብ የሚደረገው ጥረት በጣም የሚስደስት ነው። ከፖለቲካው ሌላ ስነፅሁፎች ይቀርባሉ፣ ደራሲያን ይገመገማሉ፣ የደራሲያን ስማቸው ይወደሳል፣ታሪካቸው ይነገራል።ሙዚቃዎች ይቀርባሉ። ይህ ሁሉ ታዲያ አገራችንን እንዳንረሳ፣ ባህላችንን እንዳንዘነጋ ይጠቅማል።

ለዛሬው እዚህ ላይ ላቁም። ሁላችሁም በሰላም ክረሙ ።በልጅግ